# ኤልያስ መሰረ--የስደት መንግስት ሽፍንፍን

ደረጀ ሁሴን

**ኤልያስ ክፍሌ** ራሱ በራሱ ዋጋ ያለው ፍጡር አይደለም። ቅጥረኞች እንደሚታወቀው አሽን በፈሩበት ሁኔታ ለሻዕቢያና ለባዕድ ያደረ ርካሽ ሰው ነው። በሰሞኑ ግን በብርሃኑ መዋ የዋሺንግተን ቴሌቪዥን በብርሃኑ ነጋ የረጅም ጊዜ ጓደኛ--ጌዴዎን ጊንግሬች--ቃለ ምልልስ አድርጎ ራሱን አጋልጧል።

ለዘነጋችሁት ቀደም ሲል ኤልያስ ክፍሌ ኢትዮጵያን ሬቪው የሚል መፅሄት እያወጣ ለፀረ ኢትዮጵያው ፖል ሄንዚ መድረክ ሰጥቶ የሻዕቢያን ቀይ ባሕር አሳታሚ/ ሬድ ሲ ፕሬስ/ ያስተዋውቅ ነበር። ሻዕቢያነቱን ሽፍኖ ግን ፀረ ሻዕቢያ ነኝ በሚል ጨምበል ተሸፍኖ በተለይ ኢሕአፓን በሻዕቢያ ወዳጅነት፤ በሶማሊያ ደጋፊነት ወዘተ ሲወነጅል ነበር። ከዚያም ተግባር የሚል የራሱ የጥቂቶች ቡድን መስርቶ የኢዴፓ ደጋፊ ነኝ እያለ የህብረት ምስረታውን ጥረት አጥብቆ ተቃወመ ። የሚያጠቃቸውን ደግሞ በሻዕቢያነት መክሰስ ልማዱ ነበር--የሰለጠነ ሰርጎ ገብ፤ በጥባጭ። ህብረቱ (ኢዴኃኅ) ሲመሰረት ደግሞ ከመድረክ "ጠፍቶ" ከርሞ ከዚያ ደግሞ እንደገና በመፅሄቱ ስም ድረ ገፅ ይዞ ብቅ አለ ። ልደቱ ክህደቱን ዳግም ሊጭንብን ተፍጨረጨረ--አልሆነለትም። ከዚያም የቅንጅት ደጋፊ ነኝ ብሎ ሌሎች ድርጅቶች ላይ ዘመተ --የመከፋፈል ስራ ተልዕኮ ይህ ነው። በአጭር ጊዜ የቅንጅት መሪዎች ላይ ሴራ ጎንጉኖ መወንጀል ጀመረ ። ሳይውል ሳያድርም በኤንጂነር ኃይሉም ላይ የጭቃ ጅራፉን አጮኸ። የብርቱካንና ብርሃኑ ነጋ ዋና ደጋፊ ነኝ አለ ። ከሁሉም ግን ላላወቁት ያስገረመው ይህ መሰሪ ግለሰብ በይፋ የሻዕቢያ ደጋፊ፤ ይህ ብሄረሰብ አትበሉ ባይ የነበረ የተገንጣዩ ኦነግ አፈቀላጤና የኦጋዴን ተገንጣዮች ወዳጅ፤ ይህ ፀረ ሶማሌ ነኝ ባይ የሶማሊያ እስላማዊ ፅንፈኞች ዋና ጠበቃ ሆኖ ብቅ አለ ። የትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ደጋፊ ነኝ በሚልም የሻዕቢያን ግብ ለማሟላት ተንቀሳቀሰ ። ዛሬም የብርሃኑና አንዳርጋቸው ግንቦት 7 የተባለው ቡድን ዋና ደጋፊ ሆኛለሁ ብሎ የሻዕቢያን ዓላማ ሊያሟላ ይሰራል።

ከላይ በተጠቀሰው የዋሺንግተን ቴሌቪዥን ባደረገው ቃለ መጠይቅ ( በነገራችሁ ላይ ይህ ቴሌቪዥን በብርሃኑ መዋ ስር ሲሆን ጠያቂውም የብርሃኑ ጓደኛ በመሆኑ ያው እርስ በርሳቸው ተጠያያቁ ማለቱ ይቀላል) ኤልያስ ክፍሌ ያበጠው ይፈንዳ ብሎ የሻዕቢያ ቅጥረኛነቱን አጋልጧል። የአሁኑ ስራው ግን በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የስደት መንግስት ይቋቋም በሚል ሽፋን ነው። የዚህ መንግስት አባላትም እነ ዶክተር-(ኮለኔል?) ብርሃኑ ነጋ፤ ኦነግ፤የኦጋዴን ግንባር (በዚያድ ባሬ የባህር ህይል አዛዥ የሚመራው)ና የአርበኞች ግንባር መሆናቸውንም ይህ የሻዕቢያ ቅጥረኛ ተናግሯል። በዚህ አላበቃም። የኢትዮጵያን አንድነት የብሄረሰብ መብት አወቅን በሚል ሳዱት ብሎ የአዞ እምባ ያነባ የነበረው ይህ ሰላይ ዛሬ የተገንጣዩ ኦነግ ዋና ደጋፊ ሆኖ በዚሁ ቃለ ምልልስ ላይ የኦነግን ዴሞክራሲያዊነት (ከሁሉ የበለጠ ነው ብሏል) ለማስረዳት ደፋ ቀና ሲል ኦነግ ልዩ ክፍሎችና ኮሚቴዎች እንዳለው ተናግሮ የራሱን ክስረት አጋልጧል። ደርግስ ወያኔስ መች ኮሚቴ አነሳቸው? መሰሪው ኤልያስ በግልፅ ኦነግን የሚደግፈው በሻዕቢያ ትዕዛዝ ነው ማለት አልቻለም። ቢሆንም ግን ሻዕቢያ በድርጅቶች ጉዳይ መቸም ቢሆን ጣልቃ አይገባም ሲል አስቆናል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የሶማሊያ ተቃዋሚዎች አስመራ አሉ ግን ሻዕቢያ በውስጥ ጉዳያቸው አልገባም ብሎ ሲቀባጥር የሶማሊያው ድርጅት አንዱ መሪ--አስመራ የነበረው ሼክ አህመድ-- ከጅቡቲ በሰጠው መግለጫ ሻዕቢያ በጉዳያችን ጣልቃ እየገባ መበጥበጡን ያቁም ሲል በይፋ ጠይቋል። የኤልያስ የቅጥረኛነት ወንጀል በተለይ በዚህ ቃለ ምልልስ ብቅ ያለው ሻዕቢያ በአርበኞች ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ እነ ተስፋዬ ጌታቸውንና ሌሎችን መግደሉን ውሸት ነው ብሎ በመካዱ ነው፡ ከዚህ የበለጠ ፀረ ኢትዮጵያዊነት ሊታሰብስ ይችላል?

የኤልያስ ተልዕኮ ምንድነው? በቅድሚያ ከነብርሃኑና አንዳርጋቸው ጋር ሆኖ ፀረ ወያኔ የትጥቅ ትግልን ጥረት ማደናቀፍ ነው። በብርሃኑ ነጋና አንዳርጋቸው /ዝነኛ ቡቡዎች/ የሚመራ የሽምቅ ውጊያ መቸም ሊኖር ይችላል ብሎ መገመት ቅዠት ነው። ግንቦት 7 በእውነቱ ግንቦት 20 ለመሆን 13ም አይፈልግም። ወኔዋም ልቢቷም የለችምና የእነዚህ ጦረኞች ነጋሪት ግሶማ ዓይጢቷንም አያስበረግግ። ሌላው የአልያስ ተልዕኮ በኢሕአፓ ላይ መዝመት መሆኑን በድረ ገፁ አሳይቷል። ዛሬ በብርሃኑ ነጋ ቡድንና በፀረ ኢሕአፓ አንጃዎች መካከል የውስጥ ውስጥ ግንኙነት መጀመሩንን በእነ ብርሃኑ ድረ ገፆች ማየት ይቻላል። ይህ ትስስር ደግሞ ፀረ ሻዕቢያ ነኝ ብሎ የሚምለውን አንጃ ወደ ኤርትራ ይወስደው ይሆን? በድረ ገፆች ቅ ቅ ቅ ቅ ቅ የሚባለውን ያስታውሰናል።ኢሕአፓን ማጥቃትና ማዳከም ደግሞ ለፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ዋና ስራ መሆኑ ከታወቀ ጊዜ አልፏል። ቀጥሎም እነ አባ ጃፋርና ሌሎች ቀና ሀሳቢዎች የስደት መንግስት/ሽግግር መንግስት ያሉትን ለማክሸፍና የፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎችን ጥምረት በሻዕቢያ ስር ለመመስረት ነው። ኤልያስ ከዚህ በተጨማሪ ክስረት ያጋጠመውን ኦነግንም በላያችን ሊጭን ተነስቷል። ኦነግ ነፃ ኦሮሚያን እመሰርታለሁ፤ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብሎ እየቀጠለ ሀገር ወዳድ በሉኝ ባዩ ኤልያስ ለምን በጭፍን ይደግፋቸዋል? በሻዕቢያ ስለታዘዘ። ኤልያስ ሀገር ወዳድ ሳይሆን በጥባጭ ፀረ ኢትዮጵያ ግለሰብ ስለሆነ ። እስከመቸ ታዲያ ይህ አደገኛ የባዕድ ቅጥረኛ ዝም ተብሎ ይታያል?

በአሁኑ ጊዜ የወያነ አገዛዝ ተቃዋሚዎችን ከፍሎና ከፋፍሎ ለማውደም የጀመረውን ሴራ በእጅ አዙር በስራ የሚያውሉት መሰሪዎች ዛሬ በአገዛዙ ላይ ትጥቅ አወጅን የሚሉን አስቂኝ ኮማንደሮችና አንጃዎች መሆናቸውም ምስጢር አይደለም። ኤልያስ ክፍሌ የሻዕቢያን ጥቅም አስቀድሞ ግን ሀገር ወዳድ መስሎ እነ ብርሃኑና አንጃዎችንና ኦነግን አቅፎ ለኢትዮጵያ ውድቀት እየሰራ ነው። ተባባሪዎቹ ደረ ገፆች ሆኑ ሚዲያዎችም መታወቅና መጋለጥ አለባቸው። አቶ አንዳርጋቸው አፍ አምልጦት “ኤሊሚኔት እናረጋችኋለን” ብሎናል። ከቻለ ይሞክር! የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በርካሽ የሻዕቢያ ና የወያኔ ቅጥረኞች ተሸናፊ አይሆንም። የኢትዮጵያ ልጆች ተባብረው ቅጥረኞችን ጥግ ያስይዛሉ።

ድል ለሕዝብ!

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com